# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 ቿፍትሕ፣የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ሳምንታዊ ልሳን፤

www.ginbot7.org

ቁጥር 25 ጥቅምት 27 2001 ዓ.ም

አንብበው
ያስነብቡ !
አባዝተው
ያሰራጩ !

ከግንቦት7 :ንቅናቄ የተሰጠ ጋዜጣዊ መግለጫ:

## የማንረሳው ወንጀልና የማንረሳቸው ሰማእታት

የዛሬውን እለት የተለየ የሚያደርገው በወርሃ ጥቅምት በ22ተኛው ቀን 1998 አ.ም ዘረኛውና አምባገነኑ መለስ ዜናዊ፣ እንደውርዴ በውርስ በተላለፈለት ጸረ ኢትዮጵያዊነት ጭካኔ፣ እንደ አያቶቹ ጌታ፣ እንደ ግራዚያኒ የሃገሪቱን ንጹህ ዜጎች ደም በከተሞችና በገጠሮች በግፍ ያፈሰሰበት እለት መሆኑ ነው::

ይህን ቀን በተለየ እንድናስታውሰው የግድ የሚለን በእዚህ ቀን መለስ ዜናዊ፣ ህዝብ በግንቦቱ ምርጫ የቀማውን የመንግስት ስልጣን በሃይል ይዞ ለመቀጠል ወስኖ የንጹሃን ደም በሃገሪቱ እንደጎርፍ እንዲፈስ የወሰነበት፣ በመቶዎች የሚቆጠሩት እንደአውሬ በመትሬ ተኳሾች ታድነው ያለቁበት፣ በሽዎች የቆሰሉበት፣ በአስር ሽዎች የሚቆጠሩት ደግሞ ከየቤታቸው እየተለቀሙ ከዘረኛነት ብቻ በሚመጣ ጭካኔ እየተቀጠቀጡ ያለውሃ፣ ያለምግብ፣ ያለመጸዳጃና ያለህክምና፣ ወገንና ዘመድ ልብስና ስንቅ ሊያቀብሏቸው በማይችልባቸው የበረሃ የማጎሪያ ጣብያዎች የተጣሉበት፣ በወባ፣ በዱር አውሬ በአዞ በርካታዎች ህይወታቸው የተቀጠፈበት፣ ቁጥራቸው ከተገደሉት፣ ከቆሰሉትና ለእስር ከተዳረጉት በብዙ እጅ የሚበልጡት ደግሞ፣ እራሳቸውን ከአራት ኪሎ ቤተ መንግስት ውስጥ በፍረሃት፣ በዘረኛ ጥላቻና በስልጣን ሱስ ተለክፎ ከሚያጓራው የአበደ ውሻ የጥፋት መልእክተኞች ንክሻ ለማትረፍ፣ ከቤተሰባቸው፣ ከልጆቻቸው፣ ጧሪ ቀባሪ ከሌላቸው ወላጆቻቸው ተለይተው፣ ከቀያቸው ከመንደራቸው ተፈናቅለው፣ የጅምላ ስደት በየአቅጣጫው የጀመሩበት እለት ነው:: ከእነዚህ መሃል ካሰቡበት የሰላምና የርጋታ የስደት መዲና ሳይደርሱ ባህርና በረሃ በልቷቸው የጥንብ አንሳና የሻርክ እራት ሆነው የባከኑትን ነፍሶች ቤቱ ይቁጠረው እንዳንል፣ ቤቶቻቸውም የየትኞቹ አጥንት ባህር ወለል ላይ እንዳረፈ የየትኞቹ ደግሞ የበረሃ አሸዋ እንደለበሰ አያውቁም::

ይህ እለት የኢትዮጵያ ሃገራችንና የዜጎቿ ሁሉ የመከራና የጭንቅ፣ የጦርነትና የረሃብ የነበሩ አስከፊ የታሪክ ምእራፎች ተዘግተው፣ ሃገራችን ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ በሆነ የፖለቲካ ስርአት ላይ ቆማ፣ ፈጣን የሆነ ማህበራዊና ኢኮኖሚያ ግስጋሴ ውስጥ ትገባለች ብለው ሚሊዮኖች የተሸከሙት ተስፋ በመለስ ዜናዊ ጸረ-ኢትዮጵያና ጸረ ሕዝቧ ጨካኝ ትእዛዝ የተነነበት፣ ብሩህ ህልማቸውን ወደ አስከፊ ቅዠት የተቀየረበት፣ በሃገሪቱ ከተሞችና ገጠሮች ሰማይ፣ ጨለማ በቀትር እንዲከሰት የተደረገበት እለት ነው::

በሃገራችን ታሪክ ህዝብ በየግዜው በሃገር ውስጥ በበቀሉና ሃገር አቋርጠው በመጡ አምባገነኖችና ፈላጭ ቆራጮች ማለቂያ የሌለለው ግፍና እልቂት ሲደርስበት ሲዋረድና ሲፈናቀል ኖሯል:: አበሳና ጭንቅን ከሚለብሰው መጨቅጨቂት ድርና ማግ ጋር ሸምኖ ሲለብስ፣ ከሚበላው ቆሎና ጥራጥሬ ጋር ቀላቅሎ ሲቆረጥም፣ ከሚተኛበት ቁርበት ስር አንጥፎ፣ ከላይ በትኋን ከታች በጣርና በሲቃ፣ እንደገና ዳቦ ሲለበለብ የኖረ ነው:: ይሁንና በታሪካችን ከተካሄዱት አሰቃቂ የጭፍጨፋ ታሪኮች በሙሉ በመለስ ዜናዊ ትእዛዝ የተካሄደውን ግፈኛ ድርጊት የሚወዳደረው የለም:: ይህን የምንለው ያለምክንያት አይደለም::

የውጭ ወራሪዎች፣ የውጭ ወራሪዎች ናቸውና አልገዛ ባለው የኢትዮጵያዊ ህዝብ ላይ ከሰማይ የመርዝ ጢስ ቢለቁ፣ ቦንብ ወረወራችሁብኝ ብለው በከተማ ያገኙትን የተማረ ሰው ሁሉ ለቅመው ቢፈጁ አያሰደንቀንም:: ግራዚያኒ ወራሪ ብቻ ሳይሆን በፋሽታዊ ርእዮተ-አለም የሚመራ ወራሪ ነበርና በየአመቱ በወርሃ የካቲት የምናሰበውን የሃዘን ቅረስ ትቶልን በማለፉ አንገረምም::

ነገስታቱ፣ መሳፍንቱ፣ መኳንንቱንና ባላባቱ ህዝብን በእሳትና

ወደገጽ 4 ዞሯል

## “ ኦባማ ፕሬዚዳንት ሆኑ!”

### ለዓለማቀፋዊ የዲሞክራሲ ትግል፤አዲስ ምዕራፍ ይከፈታል ተብሏል

ላለፈው አንድ ዓመት የመላው ዓለምን ቀልብ ሰቅዞ የቆየው የ አሜሪካ ፕሬዚዳንታዊ ምርጫ ፉክክር፤ ትናንት እኩለ ሌሊት ላይ ፍፃሜ አገኘ።ትንቅንቁ ባየለበት በመጨረሻው ቀን ሰላማዊ ጦርነት ነበር፤የዴሞክራቱ ዕጩ ጥቁር አሜሪካዊው ባራክ ስቲፈን ኦባማ ወደ ዋይት ሀውስ መገስገሳቸውን የሚያመላክቱ ፍንጮች የታዩት።ይህ አስደናቂ የፍቅር መንፈስ እስከ ኢትዮጵያ ገጠሮች ድረስ መዝለቁ የተዘገበ ሲሆን፤ስሞኑን በኢትዮ ፎረም ድረ ገፅ በፎቶ ተደግፎ የተዘገበውና ጎጃም ውስጥ በደብረ ማርቆስ መንገድ ላይ “ባራክ ኦባማ ካፌ” መከፈቱን የሚያሳየው ዜና የብዙዎች መነጋገሪያ ሆኗል።

እንደውም “ዲሞክራሲን ሊያከብሩ የማይችሉ መንግስታት፤ ለፀረ ሽብርተኝነት ዘመቻው አጋር ሊሆኑ እንደማይችሉ” እቅጬን አሳውቀዋል።ይህ አቋማቸው እንደ ኢትዮጵያ ላሉ አምባገነን መንግስታት ጀሮን ጭው የሚያደርግ መርዶ ሲሆን፤ ለብዙሀኑ ኢትዮጵያዊ ደግሞ ተሰፋ የሰነቀ የምስራች ሆኗል።

ገዥው ፓርቲ ኢህአዴግ በድረ ገፁ አይጋ ፎረም ላይ ባወጣው ተከታታይ ፅሁፍ፤ ከ ኢትዮጵያውያኑ ጋር የጠበቀ ግንኙነት አላቸው ያላቸውንና የ ኦባማ ምርጫ አስተባባሪ ኮሚቴ የሆኑትን አፍሪካ አሜሪካውያኑን የምክር ቤት አባል ኮንግረስ ማን ዶናልድ ፔይንንም፤ ክፉኛ ወቅሷል።ሆኖም፤ ይህ መሰረተ ቢስ ወቀሳ፤ በአየር ላይ ሚስማር እንደመምታት ይቆጠራል ሲሉ አስተያየታቸውን የሰጡ የፖለቲካ ተንታኞች፤ የኦባማ መመረጥ አምባገናዊ አገዛዝን ስር ነቀል በሆነ መልኩ ወደ ዲሞክራሲያዊ አስተዳደር ለመቀየር ለሚደረገው ዓለማቀፋዊ ትግል አዲስ ምዕራፍ መክፈቱ ሳይታለም የተፈታ ሀቅ ነው ብለዋል።

አዲሱን ፕሬዚዳንት” እንኳን ደህና መጡ” በማለት ከልብ የተቀበለው የግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ፤ በኦባማ መመረጥ የተሰማውን ደስታ ሲያሳውቅ፤ ፕሬዚዳንቱ በቀጣዩ ጊዜያቸው፤ ቃል የገቧቸውን ታላላቅ ቁም ነገሮች ለመፈፀም በሚያደርጉት ጥረት ፤ስኬት እንዲገጥማቸው ጥልቅ ምኞቱን ይገልፃል።

## ግንቦት 7 ለፍትህ፣ለነፃነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ

## በሳምንት ሶስት ቀናት ማለትም

**ማክሰኞ፣ሐሙስና ቅዳሜ ከምሽቱ 2፡00 እስከ 2፡30 ፤ በ12120 ኪሎ ኸርዝ በ25 ሜትር ባንድ ወይም በ15350 ኪሎ ኸርዝ በ19 ሜትር ባንድ ወደ ኢትዮጵያና ሌሎች የዓለም ክፍሎች የሚያሰራጨውን የሬዲዮ ፕሮግራም ይከታተሉ።**

# ርእሰ አንቀጽ

## ኦባማ ተመረጡ፤፡ አለም ተደሰተ። የኢትዮጵያው አምባገነን ግን ሃዘን ተቀምጧል

ባራክ ኦባማ 44ኛው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት ሆኑ ። ከጃፓን እስከ ኢራን ፤ ከብራዚል እስከ ደቡብ አፍሪካ ፤ ህዝቦች ትዕይንት አደረጉ ፤ ባደባባዮች ጨፈሩ ፣ መሪዎች የመልካም ምኞት መግለጫዎችን ላኩ ። የሲቪል መብቶች ታጋይ የነበሩት የጆርጂያ ኮንግረስማን ጆን ሉዊስ "ሰላማዊ አብዮት ነው የተካሄደው፤ ጥቁር ፕሬዚዳንት ሲሆን በህይወቴ አያለሁ ብዬ ጠርጥሬም አላውቅ" በማለት ፤የጉዞውን አድካሚነትና፤ የፍፃሜውን ታላቅነት ቋጥረውታል ። በጎረቤታችን ኬንያ ፣ የአብራካቸው ክፋይ የሆነው የባራክ ኦባማ ልጅ ለዚህ ማዕረግ በመብቃቱ ፣ ሃገሬው በደስታ ፈነደቀ ። ይህን በዘረኝነት ላይ የተካሄደ "ሰላማዊ አብዮት" በቀና መንፈስ ያላዩት ግን የኛዎቹ የወያኔ ጉዶችና ፣ በቡሽ የጡት ልጅነት ስልጣን የተሰጠው የአፍጋኒስታኑ ፕሬዚዳንት ካርዛይ ብቻ ነበሩ ። ሁለቱም ለስልጣናቸው ስለሰጉ ነው ከአለሙ ተለይተው ያኮረፉት ።

"ምኒሊክ ቤተ-መንግስት ወይም ሞት!" የሚፈክሩት የወያኔ ዘረኞች፣ በስልጣን ለመቀጠል እንዲረዳቸው፣ ከኢትዮጵያ ረሃብተኛ ጉሮሮ እየነጠቁ "ዲ.ኤል.ፒ ፓይፐር" ለተሰኘ በቀኝ-አክራሪ ሪፐብሊካኑ ዲክ አርሚ ለሚመራ የጥብቅና ድርጅት በወር 50 ሺህ ዶላር ወይም 500 ሺህ ብር ይሰጡ ስለነበር፤ የሪፐብሊካኖችን ሽንፈት እንደራሳቸው ሽንፈት ነው የቆጠሩት ። ዲክ አርሚ ይከፍትላቸው የነበሩ በሮች ሊዘጉ ስለሆነ የመለስ ኩባንያ አባላት ተሸብረዋል ። በሱማሌ ያካሄዱት ጭፍጨፋ በዘር ማጥፋት ወንጀል እንዳያስጠይቃቸው ሰግተዋል ። ሌላም የሚያውቁት ቁምነገር አለ ። በመቶ የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን የአሜሪካኖችን በር እያንኳኩ "ባራክ ኦባማን ምረጡ!" እያሉ ላደረጉት አስተዋፅኦ ፣ ቢያንስ መልካም አስተዳደርና ሰብአዊ መብትን ከዕርዳታ ጋር የማቆላለፍ ፖሊሲ ባራክ ኦባማ እንዲከተሉ ሊወተውቱ የሚችሉባቸው ብዙ በሮች የተከፍተላቸው መሆኑንም ያውቃሉ ።

ወያኔ ግን ከክፋትና በባራክ ኦባማ መመረጥ ከማዘን ይልቅ፤ የተሻለ ምርጫ ማድረግ በቻለ ነበር ። አሁንም የዘገየ አይመስለንም ። ከአሜሪካ "ሰላማዊ አብዮት" የመለስ አገዛዝ ብዙ መማር ይችላል ። ወያኔ በ18 አመት ዘረኛ አገዛዙ ፤ የአሜሪካ ዘረኝነት በጥቁሮች ላይ ያደረሰውን ዐይነት ግፍና በደል አልፈፀመም ። ሊወዳደር እንኳ አይችልም ። በአሜሪካ ዘረኝነት ቦታውን ለዴሞክራሲ መልቀቅ የመገደዱን ያህል፣ በኢትዮጵያም እንዲሁ ቢሆን የሚጠቀመው ህዝባችንና ሃገራችን ኢትዮጵያ መሆኗን ወያኔ ሊረዳው ይገባል ። ከማንም በላይ ግን ተጠቃሚው ወያኔ ራሱ ነው ። የባራክ ኦባማ ማሸነፍ እንደታወቀ፣ በሺዎች የሚቆጠሩ አሜሪካውያን ነጮች ሲያነቡ ታይተዋል ። ጭቆና ለአድራጊውም ቢሆን ጨቋኝ ነው ። ሁሌም በፍርሃትና መባነን የሚኖር ርኩሰት ነው ። በኦባማ ምርጫ የጥቁሮች ሰብዕና መረጋገጥ ብቻ ሳይሆን ፣ ነጮችም ሁሌ ከሚያባንናቸው የጥቁር ፍርሃት አርነት ያወጣቸው ክትባትም ጭምር ነው ። መንታ የወረዱት የነጮች እንባዎችም አንዱ ምክንያት ፣ ይሄው ከጨቋኝነት ከሚመጣ ፍርሃትና አለመረጋጋት ነፃ የመሆን ደስታ የፈነቀለው ነው ። "ከማንም በላይ ከዴሞክራሲ ተጠቃሚው ወያኔ ነው" ስንልም፣ ከጊዜያዊ ቁሳዊ (እንስሳዊ) ፍላጎቶችና ጥቅሞች አኳያ ሳይሆን፣ ከሰብአዊ ነፃነት አኳያ መዝነን ነው ።

ከአሜሪካ ዘረኝነት ይልቅ፣ የወያኔ ዘረኝነት የበለጠ አርነት ይወጣል ብለን ብንናገርም ተገቢ ይመስለናል ። የአሜሪካ ዘረኝነት ከ75 በመቶ በላይ የነጮች ድጋፍ ላይ የተመሰረተ ስለነበር፣ ፍርሃቱና አለመረጋጋቱ መለስተኛ ነበር ። የወያኔ ግን፣ የሃገሪቱ ዜጎች 6 በመቶ በሆነ በሃገሪቱ ሰሜናዊ ጫፍ ላይ በተገነባ ውሁድ ህዝብ ስም የሚካሄድ በመሆኑ ፣ ፍርሃቱም ጥልቅ አርነቱም በዚያው መጠን ሰማየ ሰማያትን የመጠቀ ነው ።

ከትናንት በስቲያ በባርነት ሲሸጡ ሲለወጡ የነበሩ ጥቁሮች ዛሬ ለአሜሪካ ፕሬዚደንትነት መመረጥ ከቻሉ፣ በሃገራችን ኢትዮጵያም ለአስርተ-መቶዎች አመታት እየተፈራረቀ ሲገዛ የኖረው የአማራና ትግሬ ልሂቅ፣ የኢትዮጵያ ህዝብ ፍላጎት እስከሆነ ድረስ፣ ቦታውን ለደቡቡም ፣ ለኦሮሞውም፣ ለአኝዋኩም ለመልቀቅ ፈቃደኛ የማይሆንበት ምንም ምክንያት የለም። በእንዲህ አይነቱ ምርጫም በጠመንጃ የነገሰ ሳይሆን በህዝብ ምርጫ የተመረጠ መሪ ከአድዋም ስልጣን የሚይዝበት እድል ዝግ አይደለም። የሚመረጠውም በኢትዮጵያውያን አብላጫ ድምጽ በመሆኑ ከአድዋ ውጭ ሲወጣ ጥላውን እያዩ ከመንበቅበቅ ነጻ ይሆናል። ነፃነትና እኩልነት ዘመኑ ያመጣው አውሎ ነፋስ በመሆኑ፣ አብሮት መንፈስ እንጂ ከፊቱ እንደ ጋሬጣ መገተር አላዋቂነት ነው እንላለን ።

## የአሜሪካን ምርጫና ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ትምህርት

ከገጽ 4 የዞረ

እኔም በጊዜው የኦባማ መመረጥ ለአሜሪካንም ሆነ ለመላው አለም ሕዝብ እንዴት ሊጠቅም እንደሚችል አስተያየቴን ከነምክንያቶቼ አቅርቤአለሁ፡፡ ይህ ሁለት ሰአታት የፈጀ ስብሰባ ካለቀ በሁዋላ ለብቻዬ ስሆን ሳስብ የነበረው፤ እዚህ በሰው አገር ሆኜ ስለአገሩ ፖለቲካ፤ አንደኛውን ተወዳዳሪ ደግፌ ምንም ሳልሸማቀቅ አስተያየቴን ስሰጥ፤ ያለአገርህ መጥተህ ለምን ይህን አስተያየት ትይዛለህ ወይንም ትሰጣለህ ብሎ የጠየቀኝ አለመኖሩ ብቻ ሳይሆን ትክክል ላይሆን ይችላል ብሎ እንኳዋን ለአንድ አፍታ (ከእኔ የተለየ ሀሳብ የያዙትን ጨምሮ) ያሰበ እንኳዋን የለም፡፡ በርግጥ ዜጋ ስላልሆንኩ ድምፅ መስጠት አልችልም፡፡

ይህ ደግሞ ህጉ ነው ተገቢም ነው፡፡ በሰው ልጅነት ግን የራሴን አስተያየት የመያዝ፤ ይህንንም ለሕዝቡ በአደባባይ የማሰማት፤ የመፃፍ መብት እንዳለኝ ከጥያቄ ውስጥ እንኳዋን የሚያስገባው የለም፡፡ በገዛ አገሬ በኢትዮጵያ ግን ይሕ መብት የለኝም፡፡ እኔ የምናገረው ካልተስማማው ሊያስረኝ፤ ሊደበድበኝ፤ ሲከፋም ሊገድለኝ የሚችል ስልጣን አለኝ ብሎ የሚያስብ የጥቂት አምባገነኖች ቡድን ነው በአገሬ ያለው፡፡ ይህን ቁጭ ብዬ ሳስብ በጣም የገረመኝ፡ እነኝህ የኛ ጉዶች ምን ያህል በትእቢት የተወጠሩ ቢሆኑ ነው ሰውን በአገሩ መብቱን ከልክለው በጉልበት መግዛት የሚፈልጉት? እንዴትስ ነው ይህንን እንዲያደርጉ የፈቀድንላቸው? እንዴት ነው እንደኛ አይነት በጣም የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለው አገር ህዝብ ከአለሙ ሁሉ ወደሁዋላ ቀርተን፤ ነፃነታችንን ተቀምተን፤ አንገታችንን ደፍተን የምንኖረው? መቼስ ነው እንደዚህ አይነት ትእቢተኛ አገዛዝ ለአንዴም ለሁሌም በአገራችን የሚያበቃውና አረረም መረረም እራሳችን በመረጥነው፤ ሰውነታችንን ባወቀና መብታችንን ላለማክበር ለማሰብ እንኳዋን የማይችል መንግስት የሚኖረን? የሚለውን ነበር፡፡

በእርግጠኛነት መናገር የምችለው የነሱም የትእቢት አገዛዝ፤ የኛም የውርደት ኑሮ ባስቸኩዋይ ማብቃት አለበት፡፡ ይህን ደግሞ ማድረግ የምንችለው ሁላችንም በዚህ መልክ በፍፁም አንገዛም ብለን በግልም በጋራም ስንወስን ነው፡፡ ያ ደግሞ ነገ አይደለም፡፡ ትላንት መሆን የነበረበት ነው፡፡ የአሜሪካ ምርጫ የሚሰጠን ትምህርት እልህ ነው፡፡ በምንም አይነት ነፃነታችንን በማንም ተቀምተን ላለመኖር የመወሰንና ለዚህም በቁርጠኛነት ለመታገል የሚያነሳሳ እልሕ!

ግንቦት 7 ድምጽ በግንቦት 7 ለፍትህ ለነጻነትና ለዴሞክራሲ ንቅናቄ የህዝብ ግንኙነትና ቅስቀሳ ዘርፍ በሳምንት አንዴ የሚዘጋጅ ድርጅታዊ ልሳን

የፖስታ ሳጥን ቁጥር ፦ POBox: 4916
2003EX Haarlem
The Netherlands

# የፖለቲካ ትንተና

በዚህ አምድ ስር ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ሌሎች ጉዳዮችን የሚመለከቱ መጣጥፎች ይቀርባሉ

## የአሜሪካን ምርጫና ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ትምህርት

ከብርሃኑ ነጋ

የዘንድሮው የአሜሪካ ፕሬዜዳንታዊ ምርጫ በብዙ መልኩ ታሪካዊ መሆኑ ብቻ ሳይሆን እኛ ኢትዮጵያውያን ከገጠመን የአገዛዝ ፈተና አንፃር ብዙ ልንማርበት የምንችለው ነው፡፡ በእርግጥ እኛና እነሱ በብዙ ጉዳዮች እንለያያለን፡፡ ስለዚህም እነሱጋ የሆነው ከእኛ ሁኔታ ጋር በቀጥታ ይገናኛል ማለት አይደለም፡፡ እነሱ ሀብታሞች ናቸው፡፡ እኛ አይደለንም፡፡ እነሱ አዲስ አገር ናቸው፡፡ እኛ በጣም የረጅም ጊዜ ታሪክ ያለን ነን፡፡ እነሱ ከችጋርና ከጭቆና ሸሽተው ከተለያየ አገር መጥተው በቅርብ ጊዜ በስደተኝነት የመሰረቱት አገር ነው፡፡ እኛ ልንቆጥር ከምንችለው ጊዜ በላይ በዚሁ አካባቢ ነበርን፡፡ የሰው ልጅ ትውልድ መጀመሪያ ነን ነው የምንለው፡፡ ይህንን አገር አገራቸው ለማለት በተወላጆቹ ላይ አያትና ቅድመ አያቶቻቸው ብዙ በደል ፈፅመዋል፡፡ ብዙ የአፍሪካ ወንድሞቻችን በባርነት ተሸጠው ስቃያቸውን በልተዋል፡፡ የነሱ ተወላጆች ደግሞ እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ በዘረኛነት ተበድለዋል፡፡ ታሪካቸው እንደ ሁሉም አገር የኛንም ጨምሮ ጥሩም መጥፎም ገፅታ አለው፡፡

ከዚህ ሁሉ የመከራና የግፍ ታሪክ ግን የነፃነትን ምንነት ተምረውበታል፡፡ የአዲሱ አገራቸው መስራቾች ከአውሮፓ አሰድዶ ያመጣቸው ድህነትና ነፃነት ማጣት በአዲሱ አገራቸው እንዳይደገም፤ የተረጋጋ አገር ሊሰጣቸው የሚችለው በግለሰብ ነፃነት ላይ የተመሰረተ፤ ዴሞክራሲያዊ ስርአት መሆኑን በመገንዘብ እስከአሁን ድረስ የሚኮሩበትን ሕገ መንግስት አርቅቀው በተግባር እያዋሉት ይገኛሉ፡፡ በኢኮኖሚ መስኩም መብቱና ነፃነቱ የተጠበቀ ሕዝብ ምን ሊሰራ እንደሚችል ለአለም አሳይተዋል፡፡ በሳይንስ፤ በቴክኖሎጂ፤ በአጠቃላይ በእውቀት ቀዳሚነትን ቦታ ይዞ መሄድ የሚቻለው በነፃነት ማሰብ፤ ያለፍርሀት መከራከር፤ የሚችል ሕዝብ ባለበት ቦታ መሆኑን ለመላው አለም አስተምረዋል፡፡

የሰው ልጅ ሁሉ በተፈጥሮው እኩል ነው ከሚል የአብርሆት ፍልስፍና ተነስተው የቀረፁት ሕገ መንግስት፤ የሰው ልጅ ሲሉ ጥቁሮችን፤ ሴቶችን፤ የአገሬው የመጀመሪያ ተወላጅ ሕንዶችን አይመለከት ይመስል በሕገ መንግስታቸው የሰጡትን የሰው ልጆች ዴሞክራሲያዊ መብቶች ለነኝህ የህብረተሰብ ክፍሎች በተግባር ከልክለው ለረጅም ጊዜ ቆይተዋል፡፡ የሕገ መንግስታቸው መንፈስ በተግባር በደቡቡ የአገራቸው ክፍል የሚታየውን የባርነት ስርአት እንደማይፈቅድ ሲረዱ ‹ባርነት ካልቀጠለ እንገነጠላለን› ይል ከነበረው የደቡቡ የአገራቸው ክፍል ሕዝብ ጋር እጅግ የሚሰቀጥጥ ጦርነት አድርገው የአገራቸውንም አንድነት የአንድነታቸውም መሰረት የሆነውን ነፃነት ጠብቀው ለዚህ በቅተዋል፡፡ ለረጅም ጊዜ በተካሄደ ትግልና በፈጠሩዋቸው ነፃ ተቋማት ጠንካራነት ዴሞክራሲያዊ መብታቸውን በተግባር ተከልክለው የነበሩትን የሕብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ አካተው ሕገ መንግስቱ የተመሰረተበትን የነፃነትና የእኩልነት መርሆ ቢያንስ በፖለቲካው መስክ እውን እያደረጉ ናቸው፡፡ ሑሉም ዜጋቸው በአሜሪካዊነቱ ተመክቶ፤ ደረቱን ነፍቶ፤ ከማንኛውም የአገሬው ሰው ጋር እኩል ነኝ ብሎ፤ እንደማንኛውም የአገሬው ሰው ችሎታው ካለው ዘሩ፤ ሀይማኖቱ፤ ቀለሙ፤ ፆታው ሳያግደው ሕዝብ እስከመረጠው ድረስ የአገሩ መሪ መሆን እንደሚችል የሚያምንበት ደረጃ ላይ ደርሰዋል፡፡ የአሁኑን ምርጫ ያሸንፋል ተብሎ የሚጠበቀው ባራክ ኦባማ የዚህ ቃል ኪዳን ውጤት ነው፡፡ አሜሪካኖች እዚህ ደረጃ ላይ የደረሱት የተለዩ ፍጡሮች በመሆናቸው አይደለም፡፡ ቀደም ብዮ እንዳልኩት እንደማንኛውም ሕዝብ የራሳቸውን ችግሮች አልፈው፤ ከራሳቸው ስህተቶች እየተማሩ፤ ወደ ሁዋላ በመመልከት ሊጎትቱዋቸው የሚፈልጉ ሀይሎች አንዳንድ ጊዜ እያሳሳቱዋቸው ግን አብዛኛውን ጊዜ ወደፊት የሚመለከተው ሀይል የበላይነቱን እያገኘ፤ ሁል ጊዜም ግን በጊዜው የፖለቲካ በትረ ስልጣኑን (government) ማን ያሸንፋል ከሚለው ይልቅ የፖለቲካው መልህቅ እንዳይበጠስ አጥብቆ የያዙትን መሰረታዊ የአገር ስምምነቶችና

ስምምነቶቹን

የሚያስጠብቁትን ተቋማት በማክበርና በመንከባከብ ነው ቀስ እያሉ እየዳበሩ እዚህ የደረሱት፡፡ የአሜሪካ የፖለቲካ ስኬት የሚያስተምረን አንዱ ነገር እንደዚህ አይነት የተረጋጋ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ለመፍጠር የተለየ ሕዝብ መሆን የለበትም፡፡ ማንም የአለማችን ሕዝብ ኢትዮጵያን ጨምሮ፤ እንደዚያ መሆን እንደሚችል ነው፡፡ ከአፍንጫው አርቆ ማየት የሚችል፤ ከዛሬው ትንሽ ፍርፋሪ ይልቅ የረጅም ጊዜ የራሱን፤ የልጆቹንና የማህበረሰቡን ጥቅም ማሰላሰል የሚችል ልሂቅ እንዲኖር ነው የሚያስፈልገው፡፡

የአሁኑን የአሜሪካ ምርጫ ካለፉት ስምንት አመታት አስተዳደራቸው ጋር ስንመለከተው የምናገኘው ሁለተኛው ትምህርት አንድ ምርጫ ጥሩ መሪ ሁሌም እንደማይሰጥ ነው፡፡ የቡሽና ቼኒን ያለፈው ስምንት አመት ታሪክ የተመለከቱ አሜሪካውያን፤ ሕዝብ ምን ያክል የተሳሳተ ምርጫ ሊያደርግ እንደሚችል አይተውታል፡፡ የቡሽ አስተዳደር በአገር ውስጥ ኢኮኖሚውን በማውደቅና መንግስቱን በታሪካቸው ታይቶ የማይታወቅ ባለእዳ በማድረግ፤ ከብዙሀኑ ሕዝብ ይልቅ ለጥቂት ጉዋደኞቹና ደጋፊዎቹ በመቆም የብዙሀኑን ሕዝብ ኑሮ በማጎሳቆል፤ በውጭ አገር የአገሪቱን ምስል በማበላሸትና ጥላሸት በመቀባት፤ የአሜሪካንን ጠላቶች በማብዛት፤ ለአምባገነኖች በመቆም…ወዘተ በዚህም ምክንያት የአሜሪካን ሕዝብም ሆነ ሚዲያ በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት በመተቸትና በማብጠልጠል እስከአሁን ቆይተዋል፡፡ አሜሪካኖች በዚህ አስተዳደር የገጠማቸውን ችግር የሚገልፁበት አንድ ምሳሌ ዛሬ ሲ. ኤን. ኤን በተባለው የአሜሪካ የቴሌቪዥን ጣቢያ የዘገበውን አሳዛኝም አስቂኝም ነገር ማስታወስ ይበቃል፡፡ በምርጫው ወቅት ከሚመረጡት የተለያዩ ተወዳዳሪዎች ሌላ በተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ሕዝበ ውሳኔ የሚፈልጉ ጉዳዮች (ሬፈረንደም) በምርጫው ወቅት ህዝቡ እንዲወስን ይቀርባሉ፡፡ ሳን ፍራንሲስኮ በተባለው ትልቅ ከተማ የሚቀርበው አንድ የውሳኔ ሀሳብ አንድ ዜጋ ወይም ዜጎች የሽንት ቤት ቁሻሻ ማፍሰሻቸውን ‹ፕሬዜዳንት ጆርጅ ቡሽ› የሚል ስም ለመስጠት እንዲችሉ የሚያስፈቅድ ሀሳብ ይገኝበታል፡፡ እንደዚህ የሚጠሉትን መንግስት አንዴ ሳይሆን ሁለቴ ተሳስተው መምረጣቸው ብቻ ሳይሆን ያለምንም ማህበራዊ ትርምስ ይህን ስህተታቸውን በሌላ ምርጫ ለማረም የሚያስችላቸው እድል መስጠቱ ነው ዴሞክራሲያዊ ስርአትን የላቀ የፖለቲካ ስርአት እንዲሆን የሚያደርገው፡፡

በዚህ ምርጫ የቡሽ አስተዳደር መልቀቁ ብቻ ሳይሆን በቦታው ለመተካት እያቆበቆበ ካለው የባራክ ኦባማ ምንነት ጋር ስናስተያየው ሌላ ጠቃሚ ትምህርት እናገኝበታለን፡፡ የአሜሪካንን ሕዝብ በዘር እንክፈለው ብንል ወደ 60 በመቶ ነጭ፤ 11 በመቶ ገደማ ጥቁር፤ ሌላ 11 በመቶ ገደማ የላቲን ዝርያ ያላቸው (ሂስፓኒክ)፤ ቀሪው 8 በመቶ አካባቢ የኤዥያ ዝርያ ያላቸው ናቸው፡፡ ሁሉም በራሳቸው ዘር ይኮራሉ፡፡ የተወሰነውና አነስተኛ የሆነው ወደሁዋላ የሚመለከተው አድህሪ ክፍል ለፖለቲካ መሪነት የሚመርጠው ሰው ከራሱ ዘር እንዲሆንለት ይፈልጋል፡፡ ነገር ግን አገሪቱ በእንደዚህ አይነት ውስጣዊም ሆነ አለም አቀፋዊ ችግር በተያዘችበት ጊዜ የአብዘኛው የዜጎች ምርጫ ችግራችንን ማን ይፈታልናል፤ ማን አስተባብሮ፤ አፋቅሮ የጋራ ችግራችንን በጋራ ጥረት እንድንፈታ ያግዘናል የሚል ለመሪነት የቀረቡትን የመምራት ችሎታ በሚመዝን መስፈርት እንጂ ማን የማን ዘር ነው ከሚል ሁዋላ ቀር አመለካከት ተመስርተው አይመርጡም፡፡ ለዚህ ነው በዘሩ 11 ከመቶውን የአገሩን ሕዝብ ከሚወክለው የጥቁር ዘር የወጣው ፤ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ሃይለ ሀሳብ

በዚህ አምድ ስር የተለያዩ ነጻነትንና ትግልን የተመለከቱ ጉዳዮች ይስተናገዳሉ

ከገጽ 1 የዞረ **የማንረሳው ወንጀልና የማንረሳቸው**

**የማንረሳው ወንጀልና የማንረሳቸው**

በብረት አቃጥለውና ፈጅተው በላዩ ላይ ቢነግሱበት፣ በግፍ ለተሰቃየውና ላለቀው ህዝብ ከሰብአዊነታችን የሚመነጭ ሃዘንና ቁጭት ቢኖረንም ነገስታቱ ከጭካኔ ሌላ ለምን ሌላ መላ አልተጠቀሙም የሚል ከታሪክ ማእቀፍ የወጣ ውንጀላ የትም እንደማያደርሰን ያንኑ ሃዘን የተሸከመ ልባችን ያውቀዋል። እንደዛም ሆኖ ነገስታቱ ለዘመናዊነትና ዘመናዊነት ይዞት ለመጣቸው ዘመናዊ የአስተዳደርና የፍትህ ስርአቶች፣ የሰብአዊና የዴሞክራሲ መብቶችና እሴቶች የቀረቡ ሆነው ሲገኙ ደግሞ የተጠያቂነትና የወንጀለኛነቸው ደረጃ ከፍ ይላል። የአጼ ሃይለስላሴ መጨረሻ ያላማረው ንጉሳዊ ፈላጭ ቆራጭነትና ዘመናዊ ታሪክ ተፋጠው መቆማቸውን ማየት ስለተሳናቸው ነበር።

እንደ መለስ ራሱን ስታሊኒስት አድርጎ፣ በምሁሩ ግፋ በለው ባይነት የስልጣን ዙፋኑን ያጠበቀው መንግስቱ ሃይለማሪያምን ብንወስድ ይህ ተራ ወታደር ምሁራኑ እንደ እድፍ ውሃ ራሳቸው ያረከሷቸውን የሰብአዊና የዴሞክሪሲ እሴቶች ለምን አልተላበሰም ብሎ መጠየቅ ለምን እባብ ርግብ የሚወጣው እንቁላል አልጣለም ብሎ መከራከር ይሆናል። በደርጉ ላለቁት ወገኖቻችን በምድራችን ለደረሰው ሲቃ ልባችን ቢደማም፣ ‹‹የስልጣንን ፉከክር በመገዳደል ብቻ ይፈታል›› የሚልን የጥፋት ርእዮተአለም በልቡ ቋጥሮ እርስ በርሱ ለመጠፋፋት በውሃ ቀጠነ የሚፈላለግ ምሁር፣ ራሱንና ነጻ አወጣዋለሁ ያለውን ህዝብ፣ መንግስቱ ሃይለማሪያም በሚባል ዘንዶ አስበልቶ በማለፉ መገረም እንደሌለብን ጭንቅላታችን ይነግረናል።

የመለስ ዜናዊን ግፍ ከሁሉ የሚያገዝፈው ግፉ የተፈጸመበት ዘመን፣ የግፉ አፈጻጸም ነው። ግፉ የተፈጸመው በንጉስነት እብሪት፣ በስታሊን አምልኮ በተደፈነ ህሊና ህዝብ መፍጀት ነውር አድርገው የማያዩ አምባገነኖችና የእነዚህ አማባገነኖች የአገዛዝ እምነት ከታሪክ ቆሻሻ በተጣሉበት ወቅት የተፈጸመ መሆኑ ነው። የዜጎች ነጻነትና መብት መከበር የዘመኑ የፖለቲካ ስርአቶች መደላድል እንደሆነ ከነቶኒ ብሌየር ጋር የአፍሪካው ዴሞክራት የሚባል ስም ተሰጥቶት ይውል የነበረው መለስ ዜናዊ ቀርቶ፣ ከስልጣኔ ርቆ ጫካና ደን ውስጥ የሚገኝ የሰው ልጅ እንኳን በሚያውቅበት ዘመን ላይ የተፈጸመ ወንጀል በመሆኑ ነው። ከሁሉም በላይ መለስ ዜናዊ ‹‹ እንከን የለሽ›› አደርገዋለሁ በማለት በአደባባይ ቃል ገብቶ፣ ህዝብ አርፎ ከተቀመጠበት ቤቱ ተጎትጉቶ ወጥቶ በተደረገ ምርጫ ስለተሸነፈ ብቻ የተፈጸመ ወንጀል መሆኑ ነው፤ ወንጀሉን የከፋ፣ ጭፍጨፋውን አሰቃቂ የሚያደርገው።

ከሁሉም በላይ በጥቅምት 22 1998 የተካሔደውን ጭፍጨፋ በሃገራችን ታሪክ ከታዩት በሙሉ አስከፊ የሚያደርገው፣ መለስን ከስልጣን ውረድ ያለው በሌለበት፣ መለስ ዜናዊ በምርጫ እንደተሸነፈ እየታወቀ ትንሽ ተጨማሪ መብቶች ስጠንና ሌላ አምስት አመት ግዛ ተብሎ በተለመነበት፣ 17 አመት ሙሉ መለስ ዜናዊ በህዝብና በሃገር ላይ በደል ሲፈጽም፣ እንደነገስታቱና እንደ ደርጎቹ ዘመን አንድ ቀን በራሱና በጀሌዎቹ ላይ የጥቃት እርምጃ ባልተሞከረበት፣ ምንም አይነት ሰበብ በሌለበት ሁኔታ የተፈጸመ መሆኑ ነው። ጥቅምት 22 1998 ለዴሞክራሲ ስርአት ማበብ ጠቃሚ የሆኑ ነጻ መንግስታዊ ተቋማት ይመስረቱ የሚለውን ፍለጎቱን ለማሰማት የተነሳው ህዝብ፣ መትረየስ፤ ሞርታር፤ ፈንጂና ክላሽ የታጠቀ አልነበረም። ጭካኔ የተሞላው ጭፍጨፋ የተካሄደው፣ የመኪናውን ጡሩምባ በመንፋት ከስራ ቀርቶ እቤቱ በመቀመጥ በራሱ በመለስ ዜናዊ ህግና ህገ መንግስት የተደነገጉለትን መብቶች በሰላማዊ መንገድ በተጠቀመ ህዝብ ላይ ነው።

ይህ ሁሉ ተደምሮ ነው የመለስ ዜናዊን ጭፍጨፋ በሃገራችን እስከዛሬ ከተፈጸሙት ግፎች ሁሉ የከፋ የሚያደርገው። የመለስ ወንጀል የሚሰራውን በሚያውቅ፣ በጭፍን ዘረኝነትና ጸረ ኢትዮጵያዊነት ስሜት በሰከረ ግለሰብ የተፈጸመ ነው። ይህን ቀን ስናስታውስ ዘረኛው መለስ በሰላማዊ ዜጎች ላይ በእብሪትና በቂመኛነት በመፈጸመው ወንጀል ከመጠየቅ የማያመልጥ መሆኑን እናውቃለን። መለስ ዜናዊና ኩባንያው በትእዛዙ ያስገደሏቸውን ሰማእታት በረሃብ እንደሚያለቁት ወገኖቻችን የቁጥር ጨዋታ ተደርገው እንዲታዩ ይፈልጋሉ። ‹‹ከእዛም በላይ ቁጥር ያለው ህዝብ በተለያዩ መንግስታት አልቋል በማለት ወንጀሉን የቁጥር ንጽጽር ለማድረግ ይዳዳቸወል።››

በዛሬው ቀን ሰማእታቶቻችንን ስናስብ የወደቁት ስም ያላቸው፣ የሚወዷቸው ቤተሰቦች፣ ጓደኞች ያሏቸው፣ ህጻናት፣ ጎልማሶች፣ ባለቴቶች፣ አረጋውያን፣ ወንድ፣ ሴት፣ ከሁሉም ብሄር ከሁሉም ሃይማኖት፣ እንደ ቀስተዳመና ህብረ-ቀለም የተቀላቀሉ የሰው ዘሮች መሆናቸውን ለራሳችንና ለገዳዮቻቸውም በመንገር መሆን ይኖርበታል። ቁጥር አይደሉም። ከወደቁት ማሃል በመዝገብ ስማቸው ሰፍሮ ያገኘናቸውን ወይም ስማቸውን የምናስታውሳቸውን ሰማእታት ሁላችንም በያለንበት በስማቸው በመጥራት እናስባቸው።

‹‹ስጋችንና ደማችን መቼም የማንረሳችሁ አካላችን፣ የተስፋችንና የህልማችን ክፋይ ናችሁ። የወደቃችሁለትን ብሩህ ህልም የትንሳኤያችሁ ምስክር ይሆን ዘንድ፣ የፈለገውን ፈተና፣ ያሻውን መስዋእትንት ቢጠይቅ በሃገራችን ፍትህ፣ ነጻነትና ዴሞክራሲ እንደምናሰፍን ቃል እንገባላችኋለን›› እንበላቸው።

**የአሜሪካን ምርጫና ለኢትዮጵያ የሚሰጠው ትምህርት** ከገጽ 3የዞረ

(ያውም ኬንያዊ አባት ያለው) ባራክ ኦባማን ለመምረጥ በተለይ ወጣቱ ትውልድ በታሪካቸው ታይቶ በማይታወቅ ስሜት እየተንቀሳቀሰ ያለው፡፡ ይህ ለእንደኛ አይነት አገር ትልቅ ትምህርት ይሰጠናል ብዬ ተስፋ አደርጋለሁ፡፡

በመጨረሻ በትምህርት ደረጃ ለማንሳት የምፈልገው ከዚህ ምርጫ ጋር በተያያዘ ካየሁት ከራሴ ልምድ በመነሳት የዴሞክራሲያዊነት መንፈስን ምንነት በአንድ በኩልና የአምባገነኖችን ስብእና በሌላ በኩል የሚመለከተውን ነው፡፡ እዚህ ባለሁበት ዩኒቨርሲቲ ከመስከረም ወር ጀምሮ እስከ ምርጫው ወቅት ድረስ ከምርጫው ጋር በተያያዘ ብዙ ፕሮግራሞች የዩኒቨርሲቲው ተማሪዎች፤ አስተማሪዎችና አስተዳዳሪዎች እንዲሁም የከተማው ነዋሪዎች በተገኙበት ይካሄዳሉ፡፡ በቅድመ ምርጫው ወቅት ለምሳሌ የቀድሞው ፕሬዜዳንት ቢል ክሊንተን ባለቤቱን ለማስመረጥ ትልቅ ስብሰባ እዚህ ዩኒቨርሲቲአችን ውስጥ አድርጎ ነበር፡፡ ከውጭ ከሚመጡት እንግዶች በተጨማሪ የዩኒቨርሲቲው ምሁራን ስለምርጫውና በምርጫው ወቅት ስለተነሱ የተለያዩ የፖሊሲ ጥያቄዎች አስተያየት ይሰጣሉ፡፡ ይህ ብቻ ሳይሆን ከሁለቱ ዋና ዋና ተወዳዳሪዎች የየትኛው ፖሊሲ አገሪቱን የበለጠ እንደሚጠቅማት መስመር ለይተው ይከራከራሉ፡፡

ከነኝህ ውይይቶች ውስጥ አንደኛው በአሜሪካን የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ላይ የተደረገ ነበር፡፡ በውይይቱ ላይ እኔን ጨምሮ ስድስት የምንሆን (አራቱ አሜሪካውያን ሁለታችን የውጭ አገር ዜጎች) የፖለቲካል ሳይንስና የኢኮኖሚክስ ምሁራን ተሳትፈንበታል፡፡

፤ወደገጽ 2 ዞሯል